MELCA-Ethiopia

Brot für die Welt

የገጠር ኑሮን ማሻሻል ፕሮጀክት ወረኢሉ ወረዳ











“ነባር ዘሮችን ተፈጥሯዊ በሆነ ማዳበሪያ በመጠቀም ያመረትኩት ምርት ቀድሞ የተሻሻሉ ዘሮችን ተፈጥሯዊ ባልሆነ ማዳበሪያ በመጠቀም ከማገኘዉ ምርት ሲነፃፀር የተሻለ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይህንንም ጥቅም ለማገኘት የቻልኩት መልካ ኢትዮጵያ በሚያካሂደዉ ፕሮጀክት ድጋፍ ነዉ።”

ሞዴል አርሶ አደር ጥላሁን አበበ

MELCA-Ethiopia



Building Resilience Communities and Ecosystems

መልካ-ኢትዮጵያ

መልካ-ኢትዮጵያ እንደ አዉሮፓዉያን የዘመን አቆጣጠር በ2004 የተመሰረተ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን ቀደም ሲል መልካ-ማህበር በሚል ስያሜ ይጠራ ነበረ። አመሰራረቱም በሀገሪቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ ያለዉን የብዝሀ ህይወት መመናመን እና ባህላዊ እሴቶችን ያለመጠበቅ ክስተት እና አዝማሚያ ባሳሰባቸዉ ጥቂት ኢትዮጵያዉያን የአካባቢ ጥበቃ እና የሀግ ባለሙያዎች ነዉ።

መልካ ማለት በአማርኛም ሆነ በኦሮምኛ ቋንቋ በወንዝ (ጥልቀት በሌለው ጅረት) ላይ ማቋረጫ (መሻገሪያ) ማለት ነው። ይህም እሳቤ በአካባቢ እና ባህል፣ በታዳጊዎች (ወጣቶች) እና በአባቶች መካከል ያለዉን ክፍተት እና በነባር ባህላዊ ስነህይወታዊ እና በሳይንሳዊ ዕውቀት መካከል ያለዉን ክፍተት የመሸፈን እና ግንኙነቱ የመፍጠር አስፈላጊነት የሚያሳይ ነዉ። የመልካ-አትዮጵያም ተልዕኮም እነዚህን ቁርኝቶች መፍጠር እና የማጎበር ነዉ።

መልካ-ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት በአምስት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ውስጥ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት አስተዳደር፣ ስነምህዳሪያዊ ግብርና፣ ዘላቂ የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ እና ህፃናትና ወጣቶችን ለመደገፍ በተቀረፁ የፕሮግራም መስኮች የሴቶችን እኩልነትና ማብቃትንም እንደ ሁለገብ ጉዳይ አድርጎ እየሰራ ይገኛል። በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በባሌ፣ በአዳባ፣ በግንደ በረት አካባቢዎች የሚካሄዱ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ይካሄዳሉ፣ በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ በሸካ፣ በጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በማጃንግ ዞን እና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትም በወረኢሉ የወረኢሉ አካባቢ የተለያዩ ፕሮጀክት እየተተገበሩ ይገኛሉ፡ ፡ በቤንሻንጉል ጉምዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ዉስጥም በተመሳሳይ የተለያዩ አካባቢንና ዘላቂ ልማትን ማዕከል ያደረጉ ክንዋኔዎች ተፈፅመዋል።

የወረኢሉ ወረዳ በደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር ዉስጥ ከደሴ ከተማ 95 ኪ.ሜ እና ከአዲስ አበባ ከተማ በ495 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ትገኛለች። ከዞኑ ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቡድን የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ የወረዳው አጠቃላይ የህዝብ ብዛት 127,041 ነዉ፡ ፡ ከዚህ ውስጥ 63,688 ወንዶች ሲሆኑ 63553 ሴቶች ናቸው። ወረዳው በተጨማሪ 24,782 አባወራዎችን ባካተቱ 20 የገጠር እና 3 የከተማ ቀበሌዎች የተከፋፈለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 17,029 ወንድ አባወራዎች ሲሆኑ 7,753 ደግሞ ሴት እማዉራዎች ናቸው።

የወረኢሉ ወረዳ አጠቃላይ የመሬት ስፋት 68,240 ሄክታር ሲሆን ከዚህ ውስጥ 32,329 ሄክታር የእርሻ መሬት ፣ 1,580 ሄክታር የጫካ መሬት ፣ 12,520 ጥቅም አልባ መሬት ሲሆን 3,624 ሄክታር ደግሞ የግጦሽ መሬት ነው። የወረኢሉ ወረዳን ጨምሮ የዞኑ አብዛኛው ህዝብ (ከ 90% በላይ) ኑሮዉ በግብርና ስራ ላይ የተመሠረተ ነው። በወረኢሉ ወረዳ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት፣ የእርሻ መሬት እጥረት እና የተፈጥሮ ሀብት መመናመን ለኢኮኖሚ ልማት እና ለኑሮ መሻሻል ወሳኝ ተግዳሮቶች እየሆኑ መጥተዋል። ይህን ከግንዛቤ በማስገባት መልካ-ኢትዬጵያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ በደቡብ ወሎ ዞን ወረኢሉ ወረዳ በሶስት ቀበሌዎች ዉስጥ (011፣ 06፣ 04) “የገጠር ኑሮን ማሻሻል ፕሮጀክት” የሚል ስያሜ የተሰጠው ፕሮጀክት ቀርፆ ከብሬድ ፎር ዘ ዎርልድ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከነሐሴ 2010 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል ።

የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ዓላማ በአነስተኛ የኑሮ ደረጃ ያሉ አርሶ አደሮችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ሲሆን። ፕሮጀክቱ ሁለት መሰረታዊ ስራዎች ላይ ያተኮረ ነው። አንዱ የአግሮ-ኢኮሎጂ (ስነ ምህዳሪያዊ ግብርና) ተግባራትን በማስተዋወቅ የአፈርና ዉሀ ጥበቃን በመስራት፣ ነባር ሀገር በቀል የሆኑ ዝርያዎችን ከጥፋት በመታደግ እንዲሁም ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ተፈጥሮአዊ የሆኑ ማዳበሪያዎችን በማስተዋወቅ የተፈጥሮ ሀብታቸውን በዘላቂነት እንዲጠብቁ እና ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ማህበረሰቡን ባሳተፈ መንገድ ተግባራዊ የሚያደርግ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ሴቶች ላይ ትኩረት ያደረጉ የኑሮ ማሻሻያና የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ በመመስረት የገቢ ማስገኛ ስራ ላይ የሚያተኩር ድጋፍ ማድረግ ነዉ።

ይህ ፕሮጀክት በአማራ ክልል በወረኢሉ ወረዳ በሶስት ቀበሌዎች ከ2007 ዓ.ም እስከ 2012 ዓ.ም ባሉት ሁለት መርሀግብሮች ላለፉት ስድስት ዓመታት እየተተገበረ ያለ ነዉ። በዚህም ሂደት 52 ራስ አገዝ ቡድኖችን በማደራጀት 880 የሚጠጉ ሴቶችን የብድር አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ላይ ተሰማርተዉ ገቢያቸዉን እንዲያሳድጉ እየሰራ ይገኛል፡ ፡ ከእነዚህም ስራዎች መካከል ጥሩ ተሞክሮ ያላቸዉን የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ባለታሪኮች እንደሚከተለዉ ቀርበዋል።

እድገት በህብረት ራስ አገዝ ቡድን

የእድገት በህብረት ራስ አገዝ ቡድን የሚገኘዉ በወረኢሉ ወረዳ 06 ቀበሌ ልዩ ስሙ "ሀረዎ" በተባለዉ ቦታ በሚያዚያ 27፣ 2007 ዓ.ም የተመሰረተ ሲሆን ቡድኑ 18 አባላትን በዉስጡ ይዟል። የራስ አገዝ ቡድኑ አባላት ስለ ራስ አገዝ ቡድን ምንነት፣ ስለ ስራ ፈጠራ ስለ ብድር ስርአት እንዲሁም ስለ ጤና አጠባበቅ የተለያዩ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ ተደርጓል።

የራስ አገዝ ቡድኑ አመሰራረት ሲጀምር እያንዳንዱ አባል አምስት ብር በሳምንት እንዲቆጥብ በማድረግ የተጀመረ ሲሆን አባላቱም ከራስ አገዝ ቡድኑ ብድሮችን በመዉሰድ የገቢ ማስገኛ ስራ ላይ እየተሳተፉ ይገኛሉ። በአሁን ሰአት ላይ ቡድኑ ሳምንታዊ ቁጠባዉን ወደ 20 ብር ማሳደግ ችሏል። የእድገት በህብረት ራስ አገዝ ቡድን ካፒታል ብር 80,460 የደረሰ ሲሆን ቡድኑ እስካሁን ያዘዋወረዉ ብር መጠን 316,400 መድረሱንም አባላቱ በሪፖርታቸዉ ላይ አካተዋል።

የእድገት በህብረት ራስ አገዝ ቡድኑ ለአባላቱ እስከ 10 ዙር ድረስ ያበደረ ሲሆን የብድሩ መጠን በነፍስ ወከፍ ከ200 ብር አንስቶ በአሁን ሰአት እስከ 4000 ብር ደርሷል። የቡድኑ አባላት ብድሩን ከወሰዱበት ጊዜ አንስቶ በስድስት ወር ዉስጥ የአገልግሎት ክፍያ 50 ብር በመጨመር የወሰዱትን ገንዘብ ተመላሽ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በስድስት ወር ዉስጥ ብድሩን መክፈል ያልቻለ አባል ቡድኑ ባወጣዉ የዉስጥ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ቅጣቱን ጨምሮ የሚከፍል ይሆናል።

አንድ የራስ አገዝ ቡድን አባል ብድር ስትጠይቅ ለቡድኑ ያቀረበችዉ የገቢ ማስገኛ ስራ አዋጭነት ታይቶ ይሰጣታል። በአሁን ጊዜ ላይ ከ18 የቡድኑ አባላት መካከል ስምንቱ ዶሮ በማርባት፣ ሰባቱ በግ በማድለብ እንዲሁም ሦስቱ በሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ ሥራ ላይ ተሰማርተዉ ይገኛሉ።



የእድገት በህብረት ራስ አገዝ ቡድን ሪፖርቱን በማቅረብ ላይ

የቡድኑ አባላት "የራስ አገዝ ቡድኑ የገቢ ማስገኛ ስራ ላይ እንድንሳተፉ እና ኑሮዋችንን እንድናሻሽል ከማድረጉ በተጨማሪ እርስ በእርስ በማህበራዊ ኑሯችን በደስታችንም ሆነ በሀዘን ጊዜ የመረዳጃ እድር በመመስረት እንድንጠያየቅና እንድንደጋገፍ ጥሩ የማህበራዊ መስተጋብር እንድንፈጥር አድርጎናል።" በማለት ይመሰክራሉ።

"መልካ ኢትዮጵያ ለራስ አገዝ ቡድናችን የተዘዋዋሪ ብድር ከመስጠቱም በተጨማሪ ለእያንዳንዱ አባላት ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ ሰጥቷል ይህም ደግሞ በማገዶ አጠቃቀም ፍጆታችን ላይ ከፍተኛ ለዉጥ ያመጣ ሲሆን ቀድሞ ለአንድ ጊዜ የምንጠቀምበትን የማገዶ መጠን ለሶስት ጊዜ መጠቀም እንድንችል አድርጎናል። ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዉ የማገዶ ፍጆታችንን ከመቀነሱ በተጨማሪ በጤናችን ላይ የቀድሞዉ ምድጃ ያደርስብን ከነበረዉ ጉዳት ጠብቆናል። አሁን ጭስ አያስችግረንም እሳትም አይለበልበንም" ሲሉ የቡድኑ አባላት ይናገራሉ። በቡድኑ ምስረታ ወቅት መልካ ኢትዮጵያ ለራስ አገዝ ቡድኑ 72 በጎችን መስጠቱን እና 180 ግልገሎች መወለዳቸዉን ቡድኑ በሪፖርቱ ላይ ያካተተ ሲሆን በአጠቃላይ በአሁን ጊዜ ላይ የተሸጡትን በጎች ጨምሮ 252 ደርሰዋል። የቡድኑ አባላት በተጨማሪም የጎልማሶች እና የጤና አጠባበቅ ትምህርት የተሰጣቸዉ ሲሆን ይህም በጣታቸዉ ይፈርሙ የነበሩ የራስ አገዝ ቡድን አባላት በእስኪቢርቶ ስማቸዉን መፃፍና መፈረም ችለዋል። እንዲሁም ባገኙት ትምህርት ከመሀይምነት ወደተሻለ የእዉቀት ደረጃ መድረሳቸዉን ተናግረዋል።

በተጨማሪም የራስ አገዝ ቡድኑ አባላት በአካባቢዉ በሚደረግ የማህበረሰብ ንቅናቄን በሚጠይቅ በማንኛዉም ተግባር ላይ የነቃ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ገልፀዋል። በዋናነት የችግኝ ተከላን ጨምሮ በተለያዩ የቦረቦር እና የተፋሰስ ልማት ስራዎች ላይ አባላቱ ከፍተኛ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ አብራርተዋል። በመጨረሻም የእድገት በህብረት ራስ አገዝ ቡድን አባላት አሁን ለሚገኙበት የተሸለ የኑሮ ደረጃ መልካ ኢትዮጵያ እና Bread for the World ላደረገላቸዉ ድጋፍ እና ከፍተኛ አስተዋፅኦ አመስግነዋል።





ወ/ሮ ጣይቱ የገነባችዉ አዲስ ቤቷ እና እያረባቻቸዉ የምትገኘዉ በጎች

ወ/ሮ ጣይቱ ዬሱፍ የአምስት ልጆች (3 ሴቶች እና 2 ወንዶች) እናት ናት። ሁለቱ ትልልቅ ልጆቿ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው። ወ/ሮ ጣይቱ እ.አ.አ በ2016 የተቋቋመውና 20 አባላት ያሉት የአዲስ ዓለም (ወይም አበባው ሸገን) ራስ አገዝ ቡድን አባል ነች።

ወ/ሮ ጣይቱ ልጆቿን ያለአባት ለብቻዋ በማሳደግ እና በማስተማር እጅግ ፈታኝ ጊዜ እንዳሳለፈች ትናገራለች። "የራስ አገዝ ቡድኔ ዉስጥ ከመግባቴ በፊት እና ከገሮጀክቱ ድጋፍ ከማግኜቴ በፊት ሁለት አነስተኛ መሬቶች፣ አንድ ላም እና ዶሮ ብቻ ነበረኝ። ሁለቱን የእርሻ መሬቶቼን ለሌሎች አርሶ አደሮች በማከራየት ከመሬቱ የሚገኘዉን ምርት እኩሌታበመካፈል እንዲሁም ከሴፍቲኔት በማገኛት ገንዘብ ኑሮዬን እመራ ነበር። ቀድሞ እኖርበት የነበረዉ ቤቴ በጣም ያረጀ እና ለመኖር የማይመች ነበር። " ስትል የቀደሞ ሕይወቷ ፈታኝ እንደነበረባት ትናገራለች።

ወ/ሮ ጣይቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣዉን የልጆቿን መሠረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ባልቻለችበት ወቅት እና በችግር ላይ ሆና በነበረ ጊዜ ነበር የአዲስ ዓለም (የአበባው ሸገን) ራስ አገዝ ቡድን አባል የሆነችና በምትኖርበት አካባቢ ነዋሪዎች ዘንድ በስፋት የምትታወቀዉ መሠረት የተባለች ሴት የጎበኘቻት። ወ/ሮ መሰረት ስለ ራስ አገዝ ቡድን ጠቀሜታ ለወ/ሮ ጣይቱ በማስረዳት በመጨረሻ በሳምንት አምስት ብር በመቆጠብ የአዲስ ዓለም ራስ አገዝ ቡድንን እንድትቀላቀል እንዳደረገቻት ትናገራለች።

በመቀጠልም ወ/ሮ ጣይቱ "ከፕሮጀክቱ መጀመሪያ ያገኘሁዋቸዉን ሶስት በጎች በማባርባት ሲዋለዱልኝ ስድስት ጠቦቶችን በ5,150 ብር በመሸጥ ከዚህም ካገኘሁት ገቢ እና የነበረችኝን ላም ሸጬ አዲስ ቤት ለመስራት በቅቻለሁ" ትላለች።

"የራስ አገዝ ቡድናችን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ለአባላቱ ብድር መስጠት ሲጀምር የተለያየ የገንዘብ መጠን ከራስ አገዝ ቡድኔ ተበድሬአለሁ። በመጨረሻው ዙር ብድር ብር 1,500 በመበደር የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን መስራት ችያለሁ" ስትል ትናገራለች። በአሁኑ ወቅት የአዲስ ዓለም (ወይም አበባው ሸገን) ራስ አገዝ ቡድን ሳምንታዊ የቁጠባ መጠኑን ወደ 15 ብር ያሳደገ ሲሆን እያንዳንዷ አባል 1,925 ብር ተቀማጭ ያላት ስትሆን የቡድኑ ካፒታል 38,500 ብር ላይ ደርሷል።

በመጨረሻም ወ/ሮ ጣይቱ "አሁን ያለሁበት ህይወት ካለፈዉ ጊዜ በጣም የተሻለ ነዉ። አሁን እኔ እና ልጆቼ ያለ ብዙ ችግር እና ስቃይ እየተመገብን ነዉ፣ ልጆቼን እያለበስኩ እና እያስተማርኩ ነው። ለዚህም ደግሞ መልካ ኢትዮጵያ በጣም እረድቶኛልእና አመሰግነዋለሁ" ስትል ሀሳቧን ቋጭታለች።







ወ/ሮ አያልነሽ ሙሄ

ወ/ሮ አያልነሽ ሙሄ በወረኢሉ ወረዳ ቀበሌ 06 ነዋሪ ስትሆን የኮኛ ራስ አገዝ ቡድን አባል ነች። ወ/ሮ አያልነሽ አስቀድሞ የመልካ ኢትዮጵያ ድጋፍ ከመምጣቱ በፊት እና ወደ ራስ አገዝ ቡድኑ ከመግባቷ በፊት ስለነበራት ህይወት ስትናገር "መልካ ኢትዮጵያ ወደ መንደራችን መጥቶ ድጋፍ ከማድረጉ በፊት በራሳችን መንገድ ኦሮዋችንን ለማሸነፍ ትግል ላይ ነበርን። ከባለቤቴ ገንዘብ እየጠየቅኩኝ ነበር ቤተሰቤን የማስተዳድረዉ።"

በመቀጠል "ከሦስት አራት አመት በፊት መልካ ኢትዮጵያ ድጋፍ ማድረግ ሲጀምር አራት በጎች ተገዝተዉ ተሰጡኝ በጎቼን በማርባት እና እየሸጥኩኝ ኦሮየን መደጎም ችያለሁ። እሰከ አሁን ድረስ በጎቼ ተዋልደዉልኝ 13 ግልገሎችን መሸጥ ችያለሁ። በገንዘቡም መሬት ገዝቸ ከመሬቴ ከማገኘዉ እህል እየተጠቀምኩ እገኛለሁ" በማለት አስረድታለች።

ወ/ሮ አያልነሽ ስለ ራስ አገዝ ቡድኗ ጠቀሜታ ስትናገር "በተጨማሪ ደግሞ ኮኛ ራስ አገዝ ቡድን ዉስጥ ገብቼ መቆጠብ ከጀመርኩኝ ወዲህ ደግሞ በማገኘዉ ብድር በአካባቢያችን መገበያያ በገበያ ቀን በመሆኑ እቃዎችን ከገበያ በማምጣት በመንደራችን ዉስጥ ለአርሶ አደር ማህበረሰቡ የተለያዩ ሽቀጣ ሽቀጦችን እንደ ስኳር፣ ዘይት፣ ሳሙና እና የመሳሰሉትን በመሸጥ አገልግሎት እየሰጠሁ እና የማገኘዉን ብድር የገቢ ማስገኛ ስራ እየሰራሁበት እገኛለሁ።" ስትል ትናገራለች።

ወ/ሮ አያልነሽ በመቀጠልም "እስከ አሁን ከራስ አገዝ ቡድኔ ሦስት ዙር የተበደርኩኝ ሲሆን ከህብረቱ ደግሞ 3000 ብር በመበደር ሁለት በጎችን በመግዛት ካሉኝ ጋር በመቀላቀል እያረባሁ እገኛለሁ። ሳምንታዊ ቁጠባዬን ከማረባቸዉ ዶሮዎች እንቁላል እየሸጥኩኝ 15ብር እየከፈልኩኝ ሲሆን በማገኘዉ ተጨማሪ ገንዘብ ራሴንም በማህበራዊ ጉዳይም ወላዶችን እጠይቅበታለሁ ሀዘንም አስተዛዝንበታለሁ" በማለት ገልፃለች።

ወ/ሮ አያልነሽ ስለ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ እና ጎልማሶች ትምህርት ድጋፍ ስትናገር ደግሞ "ቀድሞ ስጠቀምበት የነበረዉ ምድጃ እንኳን አይደለም ማገዶዉን እኔን በእሳት እያቃጠለ ቅልጥሜንም እያደቀቀ ነበር። አሁን ግን ፈጣሪ ይመስገነዉ በጥቂት ማገዶ እንጀራዬን እየጋገርኩኝ ነዉ ድካሜን ቀንሶልኝ እሳት ከመለብለብ አድኖኛል። እንዲሁም ደግሞ አስቀድሞ ምንም አይነት ትምህርት አልነበረኝም፤ ስሜን እንኳን መፃፍ አልችልም ነበር። ጣቶቼን በማቅለም ነበር እፈርም የነበረዉ። ሆኖም ግን መልካ ኢትዮጵያ የጎልማሶች ትምህርት መስጠት ከጀመረ ወዲህ ስሜን መፃፍ ችያለሁ ፊርማም እፈርማለሁ።" ስትል አስተያየቷን ገልፃለች።



ወ/ሮ ፋጡማ ሙሀመድ

ወ/ሮ ፋጡማ ሙሀመድ የ25 አመት ወጣት እና የሶስት ልጆች እናት ስትሆን የመልካም ራስ አገዝ ቡድንም አባል ነች። ወ/ሮ ፋጡማ ቀድሞ ስለነበራት ህይወቷ ስትናገር "በፊት ከድህነቴ የተነሳ የእርሻ መሬት እንኳ አልነበረኝም። እንጨት በመልቀም እየሸጥኩኝ ነበር ኑሮዬን የምገፋዉ። ይሄንኑ ስራዬን በመስራት ላይ እያለሁ መልካ ኢትዮጵያ በራስ አገዝ ቡድን ተደራጅተን ቁጠባ እንድንጀምር የጠየቀን። ነገር ግን እኔ በሳምንት አምስት ብር ለመቆጠብ ከቤት አምጥቼ እቆጥባለሁ በማለት ፈቃደኛ አልነበርኩም። ሆኖም ግን መልካ ኢትዮጵያ በራስ አገዝ ቡድን ተደራጅቶ መቆጠብ ምን አይነት ጥቅም እንዳለዉ በገለፀልን ወቅት በሀሳቡ አምኜበት ከማገኘዉ ገንዘብ በሳምንት አምስት ብር በመቆጠብ የመልካም ራስ አገዝ ቡድንን ተቀላቀልኩኝ።"

በመቀጠልም ወ/ሮ ፋጡማ መልካ ኢትዮጵያ ስላደረገላት ድጋፍ ስትናገር "መልካ ኢትዮጵያ አራት በጎችን ሰጥቶኝ እነርሱን በማርባት መሸጥ ጀመርኩኝ። ያረባኋቸዉን አምስት በጎች በአጠቃላይ በ11,100 ብር ሸጬ መሬት በመግዛት ከመሬቴ በማገኘዉ ምርት እራሴን እና ቤተሰቦቼን እየመገብኩኝ ነዉ። በተጨማሪ ያረባኋቸዉን በጎች በ12,100 ብር በመሸጥ አንድ ላም መግዛት ችያለሁ፡ ፡ በአሁን ሰአት አምስት ሴት በጎች አንድ ግልገል እና አንድ ወጠጤ በጎች አሉኝ። ከዚህም በተጨማሪ የራስ አገዝ ቡድናችን ሳምንታዊ ቁጠባዉን ወደ 15 ብር ከፍ ያደረገ ሲሆን እኔም ሳምንታዊ ቁጠባዬን ከማረባቸዉ ዶሮዎች የማገኘዉን እንቁላል በመሸጥ እየከፈልኩኝ ሲሆን ከቡድኔ ከማገኘዉ ብድር ደግሞ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎችን በመስራት ላይ እገኛለሁ" በማለት ትናገራለች።

"በተጨማሪ ደግሞ መልካ ኢትዮጵያ ማገዶ ቆጣቢ ምድጃ የሰጠኝ ሲሆን በእርሱም እየተጠቀምኩበት እገኛለሁ፡ ፡ በፊት ለአንድ ጊዜ እንጀራ መጋገሪያ አንድ እቅፍ እንጨት እና አንድ ኬሻ ፍግ እማግድ ነበር። አሁን ግን ትንሽ ጭብጥየ እንጨት ጣል ጣል ካደረግኩኝ እንደልቤ እጋግራለሁ። ማገዶ ቆጣቢ ምድጃዉ ማገዶ ከመቆጠቡ በላይ ከእሳት ቃጠሎ አድኖኛል። እንዲሁም ደግሞ መልካ ኢትዮጵያ የጎልማሶች ትምህርት እየሰጠን ይገኛል። በፊት የሰረታዊ ትምህርት እዉቀት አልነበረኝም። የልጆቼም ትምህርት ቤት መሄድ ይከብደኝ ነበር። አሁን ግን የጎልማሶች ትምህርት መማር ከጀመርኩኝ ወዲህ ብዙ ነገር እያወቅኩኝ ነዉ ስሜን ከነአባቴ መፃፍ ችያለሁ።" ስትል ሀሳቧን ትቋጫለች።



ወ/ሮ መሰረት አየለ እያረባቻቸዉ ካሉ ዶሮዎቿ ጋር

ወ/ሮ መሰረት አየለ የእድገት በሀብረት ራስ አገዝ ቡድን አባልና ሰብሳቢ ናት። አስቀድሞ የራስ አገዝ ቡድኑ አባል ከመሆኑዋ በፊት እና በኋላ ያላት ህይወት ስታነፃፅር እንዲህ ብላለች "ቀድሞ ስራ የለኝም ነበር። የቤት እመቤት ሆኜ ያለስራ ነበር የተቀመጥኩት። ቁጠባ ከጀመርኩኝ ቡኋላ ግን ከራስ አገዝ ቡድኔ ብድር እየወሰድኩኝ የራሴን ገቢ ማማኜት ጀምሬያለሁ። በመጀመሪያ ዙር 300 ብር ብድር ከወሰድኩኝ በኋላ ዶሮ በማርባት እየሸጥኩኝ ገቢ ማማኘት ጀመርኩ። ከዚያም ቡኋላ ተጨማሪ ብድሮችን በመዉሰድ እና የወሰድኩትን ብድር በመመለስ ተጨማሪ የሸቀጣ ሸቀጥ ንግድ ጀምሬ እየሰራሁኝ ገቢየን ማሳደግ ችያለሁ። ልጆቼንም እያስተማርኩኝ እገኛለሁ። በአስረኛ ዙር ብድር 4000 ብር ከራስ አገዝ ቡድኔ ወስጄ የተለያዩ የሸቀጣ ሸቀጥ ምርቶችን በመግዛት በአካባቢዬ ላሉ ማህበረሰብ እያቀረብኩኝ ገቢዬን ማሳደግ ችያለሁ። ብድሬንም መክፈል እንዲያስችለኝ እንዲሁም ወረት እንድይዝ ሳምንታዊ ዕቁብ ገብቻለሁ። አሁን የደረስኩበት ደረጃ እንድደርስ ገቢዬ እንዲጨምር እና ኦሮዬን እንዳሻሽል መልካ ኢትዮጵያ በጣም ደግፎኛል። ድርጅቱንም ሳላመሰግነዉ አላልፍም።"

ወ/ሮ መሰረት የራስ አገዝ ቡድኑ ከፈጠረላት የኦሮ መሻሻል በተጨማሪ በአባላቱ መካከል ያለዉ ማህበራዊ ግንኙነት ምን ያህል እንደጠቀማት ስትናገር "ይህ የብድርና ቁጠባ ራስ አገዝ ቡድን በጣም ነዉ የጠቀመኝ



ወ/ሮ መሰረት አየለ

ቀድሞ ስወልድ እንቢን የሚጠይቀኝ ሰዉ አልነበረም፡ ፡ እንዴት አደራችሁ የሚለኝ እንኪን የለም ነበር። አሁን ግን መልካ ኢትዮጵያን በጣም አመሰግናለሁ የቡድኖቼ አባላት ብወልድ ያርሱኛል፣ ቤተሰብ ቢሞትብኝ ያስተዛዝኑኛል። በማህበራችን የተነሳ ከቡድኖቼ አባላት ጋር እርስ በእርስ እንጠያየቃለን፣ እንደጋገፋለን በሀዘኑም በደስታዉም አብረን ነዉ የምንሆነዉ።"

ወ/ሮ መሰረት በተጨማሪም ስላገኘችዉ የነዳጅ ቆጣቢ ምድጃ እና የጎልማሶች ትምህርት ስትናገር "የነዳጅ (ማገዶ) ቆጣቢ ምድጃዉ ቀድሞ ስንጠቀምበት ከነበረዉ በጣም የተሻለ ነዉ። የቀድሞዉ ምድጃ በጣም ይጎዳኝ ነበር። እሳት ይለበልበኝ ነበር። አሁን ግን በአዲሱ ምድጃ መጠቀም ከጀመርኩኝ አንስቶ ራሴን አያመኝም፣ አይኔንም አይጎዳኝም፣ እሳቱም አይለበልበኝም። እንዲሁም ማገዶዬንም ቆጥቦልኛል። ቀድሞ ምንም አይነት ትምህርት አልነበረኝም ነገር ግን መልካ ኢትዮጵያ የጎልማሶች ትምህርት መማር ከጀመርኩኝ አንስቶ ብዙ ነገሮችን ማወቅ ችያለሁ። ለምሳሌ የስልክ አጠቃቀም አልችልም ነበር፣ አሁን ግን አጠቃቀሙን ከማወቄ በላይ የስልክ ቁጥሬን ፅፌ መስጠት ችያለሁ።" በማለት ሀሳቧን ደምድማለች።

እንደልቤ የነባር ዘር ማህበር

እንደልቤ የነባር ዘር ማህበር በ2011ዓ.ም እየጠፉ ያሉ ነባር ሀገር በቀል ዘሮችን ለማቆየት እና ለማባዛት በወረኢሉ ወረዳ 06 ቀበሌ ፈቃደኛነታቸዉን ባሳዩ 72 አርሶ አደሮች በ2011ዓ.ም የተመሰረተ ነዉ። ከአባላቱ ዉስጥም 24 ሴት አርሶ አደሮች እና 48 ወንድ አርሶ አደሮች ይገኛሉ።

የእንደልቤ የነባር ዘር ማህበር ሰብሳቢ የሆኑት **ሞዴል አርሶ አደር ጥላሁን አበበ** ስለ ማህበሩ አመሰራረት ሲናገሩ "ይህን ማህበር ልንመሰርት የቻልነዉ እየጠፉ ያሉ ሀገር በቀል የሆኑ የነባር ዘሮችን ለማሰባሰብ እና ወደ ምርት ለማስገባት ነዉ። ማህበሩ ከተመሰረተ በኋላ የነባር ዘሮቹን ጠብቀዉ ካቆዩ አርሶ አደሮች እና በአካባቢያችን ዙሪያ ከሚገኙ አካባቢ ገበያዎች ከመልካ ኢትዮጵያ ጋር በመሆን 8 ነባር የጤፍ እና የስንዴ ዘሮችን በ27,173 ብር በማሰባሰብ በ2012 ዓ.ም የማህበሩ አባላት ነባር ዘሮቹን በእርሻ መሬቶቻቸዉ ላይ እንዲዘሩ አድርገናል።" ሲሉ ስለ ማህበሩ ተግባር ገልፀዋል።

በመቀጠልም አቶ ጥላሁን "ማህበራችን ለአባላቱ ከተሰበሰቡተት የነባር ዘሮች ከ10ኪ.ግ እስከ 20ኪ.ግ እንደየ መሬታቸዉ መጠን አከፋፍሏል። በ2012 ዓ.ም አባላቱ በየማሳዎቻችን ላይ እነዚህን ነባር ዝርያዎች ዘርተናል፣ እያቦዛንም እንገኛለን። ምርቶቹ ከደረሱ ቡኋላ ዘሮቹን በማባዛት ከማህበሩ ከወሰድነዉ የዘር መጠን ላይ አንድ ኪ.ግ በመጨመር ተመላሽ እናደርጋለን። እስከአሁንም ባለዉ ጊዜ ነባር ዘሮቹ ከመሬቶቻችን ጋር በጣም ተስማምተዋል። በተለየ ደግሞ ተፈጥሮዊ በሆነ ማዳበሪያ የተዘሩት ነባር ዘሮች ዉጤታቸዉ የሚያረካ ነዉ፡ ፡" ሲሉ ይናገራሉ።

በተጨማሪም አቶ ጥላሁን ስለ መልካ ኢትዮጵያ ድጋፍ ሲናገሩ "መልካ ኢትዬጵያ ወደ መንደራችን ከመጣ ቡኋላ በጣም ሰፊ ስራ እየሰራ ይገኛል በተለይ ነባር ዘሮችን በማቆየት እና ተፈጥሮአዊ የሆነ የማዳበሪ አዘገጃጀት ላይ ለአርሶ አደሮቻችን ሰፊ ስልጠና ሰጥቶናል። ነባር ዘሮቹ ተጠብቀዉ መቆየታቸዉ ስላለዉ ጠቀሜታ ከመልካ ኢትዬጵያ ስልጠና ስለ ነባር ዘሮቹ እህል ጥራት፣ ጣዕምና አልሚነት የበለጠ ለማወቅ ችለናል። እንዲሁም ከኛ ቀደም በዚህ ስራ የተጠቀሙ ገበሬዎች ሲገልፁልን በዚህ በመነሳሳት ነባር ዘሮቹን ለማቆየት እና ለማባዛት ቃል በመግባት ማህበሩን ልንመሰርት ችለናል። በዚህም የመልካ ኢትዮጵያ ድጋፍ ከፍተኛ ነዉ።" በማለት ምስጋናቸዉን አቅርበዋል።





የእንደልቤ የነባር ዘር ማህበር ሰብሳቢ ሞዴል አርሶ አደር ጥላሁን አበበ በ2012 ዓ.ም የዘሩትን ነባር ሀገር በቀል የስንዴ ዘር ምርት በመሰብሰብ ላይ

“ማህበራችን በተመሰረተበት ቀበሌ 06 በርካታ አርሶ አደሮች የሚገኙ ሲሆን 72 የምንሆን አርሶ አደሮች ይህን ማህበር ልንመሰርት የቻልነዉ። የማህበራችን አባላት የሆኑ አርሶ አደሮች ነባር ዘሮቹን በመጠቀም እያሳዩት ያለዉን ዉጤት በማየት በቀበሌያችን የሚገኙ የማህበራችን አባላት ያልሆኑ አርሶ አደሮች ወደ ማህበራችን ለመግባት እንዲሁም ነባር ዘሮቹን በማሳዎቻቸዉ ላይ ለመዝራት ፍላጎት እንዳላቸዉ እየተናገሩ ነዉ።” ሲሉ የእንደልቤ የነባር ዘር ማህበር ሰብሳቢ አቶ ጥላሁን ይናገራሉ።

አቶ ጥላሁን በመጨረሻም “እኔ በግሌ መልካ ኢትዮጵያ ከሰጠን ስልጠና ቡኋላ ራሴን በማሳመን ነባር ዘሮቹን በማሳዬ ላይ ለመዝራት እና ተፈጥሮአዊ በሆነ ማዳበሪያ በመጠቀም ዉጤቱን ለማየት ወሰንኩኝ። ይሄንም ለማድረግ በራሴ በስልጠናዉ ባገኘሁት ተፈጥሮአዊ የሆነ ማዳበሪ አዘገጃጀት መሰረት ማዳበሪያዎችን በማዘጋጀት ለሙከራ ያክል በ2012ዓ.ም በመዝራት ዉጤቱን በማየት ላይ እገኛለሁ። የነባር ዘሮቹን በተፈጥሮዊ ማዳበሪያ በመጠቀም የዘራሁዋቸዉ ዘሮች ቀድሞ ስጠቀመዉ ከነበዉ ምርታቸዉ የተሻለ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።”

በተመሳሳይ **ወይዘሮ አበቡ አሊ** በ06 ቀበሌ ውስጥ በእንደልቤ ነባር ዘር ማህበር እንዲሁም በሴቶች ራስ አገዝ ቡድን ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ታታሪ ሴት ናቸዉ። ወ/ሮ አበቡ ስለነባር ዘር ባገኘችዉ ስልጠና እንዲሁም ከነባር ዘር ማህበሯ 10 ኪ.ግ የስንዴ ዘር በመዉሰድ ተክላ ነበር። በዚህም በአሁኑ ወቅት ምርትዋን በመሰብሰብ ላይ ስትሆን ነባር ዘሩ እያሳየዉ ያለዉን ዉጤት በመመልከት ደስተኛ መሆኑዋን ገልፃለች።





የእንደልቤ የነባር ዘር ማህበር ሰብሳቢ ሞዴል አርሶ አደር ጥላሁን በማሳቸዉ ላይ እና በቤታቸዉ ጓሮ ላይ ያዘጋጁት ተፈጥሯዊ የሆነ ማዳበሪያ





ወ/ሮ አበቡ አሊ በማሳቸዉ ላይ ነባር ሀገር በቀል የስንዴ ዘር በመሰብሰብ ላይ

አፈርና ዉሀ ጥበቃ ስራዎች

መልካ ኢትዮጵያ በወረኢሉ ወረዳ 04፣ 06 እና 011 ቀበሌዎች ከሚሰራቸዉ ስራዎች መካከል አንዱ የአፈርና ዉሀ ጥበቃ ስራዎችን ሲሆን በወረዳዉ ከፍተኛ የሆነ የመሬት ቦረቦሮች ይገኛሉ ከእነርሱም መካከል በቀበሌ 011 አካባቢ የነበረዉ ቦረቦርን ለአብነት ያክል ማንሳት ይቻላል። በ011 ቀበሌ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት እና በአካባቢያቸዉ የተፋሰስ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ደርብ ሀሰን የአፈርና ዉሀ ጥበቃ ስራዉ ከመሰራቱ በፊት ጎረቤር የነበረዉን ቦታ ሲገልፁት “የአፈርና ዉሀ ጥበቃ ስራዉ ከመሰራቱ በፊት ይሄ ቦታ በጣም አስቸጋሪ ነበር፤ በፊት የነበረዉ ቦረቦር (ሸለቆ) ስለማያራምድ የአንድ አካባቢዉ ማህበረሰብ ለሁለት ተከፍሎ ነበር። ሰዉ ሲሞት ቀብር እንኳን ለመቅበር ቦረቦሩ ስለማያሳልፍ አንችልም ነበር።”

የኮሚቴዉ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ደርብ የተፋሰስ ስራዉ አጀማመሩ እንዴት እንደነበር ሲናገሩ “መልካ-ኢትዮጵያ ወደ አካባቢያችን መጥቶ ይህንን ቦታ እንድናለማላችሁ ፈቃደኛ ናችሁ ወይ ብሎ ጠየቀን እኛም ፈቃደኞነታችንን በደስታ ገልፀን። አካባቢዉ ከለማ ቡኋላ የከብት ግጦሽ ክልክል መሆኑን ተስማምተን ስራዉን በከፍተኛ ጥረት በመስራታችን ቦታዉ አሁን የተሻለ ደረጃ ላይ ሊደርስ ችሎዋል።”

አቶ ደርብ ሀሰን በመጨረሻም “መልካ- ኢትዮጵያ አስቸጋሪ የነበረዉን ቦረቦር ወደ ነበረበት ለመመለስ የአካባቢዉን ማህበረሰብ በማስተባበር እንጨት፣ ፓቢዮን፣ ችግኞችን እና ድንጋይ በማቅረብ የአካባቢዉ ማህበረሰብ በጉልበቱ ታግሎ የበረቦሩን ችግር ለመቅረፍ ተችሏል። ይሄ የተሰራዉ ስራ ተጠብቆ እንዲቆይ የተፋሰስ ኮሚቴዉ የዉስጥ ደንብ አዉጥቶ በአገባመዉ አካባቢ ላይ የተከለከሉ ነገሮችን ያደረገ የአካባቢዉ ነዋሪ ቅጣት እንዲጣልበት በማድረግ የተፋሰሱን ቦታ እየጠበቅነዉ እንገኛለን።” በማለት ሀሳባቸዉን ቋጭተዋል።





በወረኢሉ ወረዳ ቀበሌ 011 የሚገኘዉ የአካባቢዉን ማህበረሰብ ለሁለት ከፍሎት የነበረዉ ቦረቦር እና መሬቱን የማዳን ስራ ላይ የአካባቢዉ ማህበረሰብ ተሳትፎ ሲያደርግ





አቶ ደርብ ሀሰን የተፋሰስ ኮሚቴዉ ሰብሳቢ፣ ወ/ሮ ዘሪቱ ሽፈራዉ የተፋሰስ ኮሚቴዉ ገንዘብ ያዥ እንዲሁም መሬቱን የማዳን ስራ ከተሰራ ቡኋላ





የ850 ሜትር እርዘማኔ ያለዉ በቀበሌ 011 አባቀሬ አገር ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ የሚገኘዉ ጎረጎር መሬቱን የማዳን ስራ ከመሰራቱ በፊት እና የአካባቢዉ ማህበረሰብ በስራ ላይ





በወረኢሉ ወረዳ 011 ቀበሌ የአባ ቀሬ አገር አካባቢ የተፋሰስ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ሱለሂማን ሀሰን እና የጎረጎር ስራዉ ከተሰራ ቡኋላ

አቶ ሱለሂማን ሀሰን በወረኢሉ ወረዳ አባቀሬ መንደር ቀበሌ 011 ዉስጥ ነዋሪ ሲሆኑ በአካባቢያቸዉ የተፋሰስ ኮሚቴዉ ምክትል ሰብሳቢ እና ገንዘብ ያዥ ናቸዉ።።

በቀበሌ 011 አባቀሬ መንደር ተብሎ በሚጠራዉ አካባቢ በመልካ ኢትዮጵያ አስተባባሪነት የተሰራዉ የአፈርና ዉሀ ጥበቃ ስራ 0.5 ሄክታር የሚሸፍን ሲሆን 850 ሜትር ርዝማኔ አለዉ። አቶ ሱለሂማን በአካባቢያቸዉ የሚገኘዉ ለበርካታ ጊዜያት የተቸገሩበት ቦረቦር በ2011ዓ.ም ከመሰራቱ በፊት ምን እንደሚመስል ሲናገሩ "ይሄ አካባቢ ቀድሞ በጣም የተበረበረ አካባቢ ነበር ከሰዉ ቁመት በሚበልጥ ርዝመት መሬቱ በጣም ተቦርቡሮ ነበር። ወደ ቦረቦሩ ከብቶች ከገቡብን እነርሱን ለማዉጣት ከፍተኛ ስቃይ ነበር። በክረምት ወቅት ቦረቦሩን ለመሻገር ባህር ዛፎችን እየቆረጥን በቦረቦሩ ላይ በማድረግ ሰዎች እና ከብቶቻችን በጊዜያዊነት ለማሻገር እንጥር ነበር።"

አቶ ሱለሂማን በመቀጠልም "ሆኖም ግን መልካ ኢትዮጵያ ወደ መንደራችን ከመጣ ቡኋላ የአፈርና ዉሀ ጥበቃ ስራዉን መስራት ችለናል የቦረቦር ስራዉ ከተሰራ በኋላ አርሶ አደሩ እና የአካባቢዉ ማህበረሰብ እፎይ ብሏል ክረምት መጣ በጋ ሆነ መሬቱ ሰላም ሆኖዋል።" "የቦረቦር ስራዉን ለመጨረስ አራት ወራት የወሰደ ሲሆን የአካባቢዉ ማህበረሰብ በጉልበቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል። መልካ ኢትዬጵያ ደግሞ ጋቢዮን፣ ድንጋይ፣ እንጨት እንዲሁም የተለያዩ የዘር ችግኞችን በማቅረብ የቦረቦር ስራዉ እንዲሰራ ደግፏል። በዚሁ አጋጣሚ መልካ ኢትዮጵያ ላደረገው ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሳላመሰግነዉ አላልፍም" ሲሉ አስተያየታቸዉን ሰጥተዋል።

በመጨረሻም አቶ ሱለሂማን "የአካባቢዉ ማህበረሰብም የተፋሰስ መሬቱ መልሶ እንዳይቦረቦር እና ወደ ቀድሞ ይዞታዉ እንዳይመለስ የተዋቀረዉ ኮሚቴ ሀግና ደንብ በማዉጣት እንዲሁም በእንጨት ቦታዉን በማጠር በመንከባከብ እና በመጠበቅ ላይ እንገኛለን።" በማለት ሃሳባቸዉን አጠቃለዋል።

MELCA-Ethiopia

Vision:

To see healthy and prosperous people that preserves their bio-cultural diversity

Mission:

To work for healthy ecosystems, resilient communities and critical young generation through developing and institutionalizing innovative approaches and experiences

Goal:

To increase the adaptive capacity to social and ecological challenges of communities and contribute to the creation of a healthy ecosystem

አድራሻ

የመልካ ኢትዮጵያ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አምባሳደር ቴያትር
ፊት ለፊት በሚገኘዉ (ዋና ፖስታ ቤት) መግቢያ አካባቢ በሚገኘዉ
ኪዳኔ በየነ ህንፃ አንደኛ ፎቅ ላይ ይገኛል።

ስልክ፡- +251-11-550-7172
ፋክስ፡- +251-11-550-4554
ፖ.ሳ.ቁ፡- 1519 ኮድ 1250
ኢሜል፡- melca.ethiopia2004@yahoo.com
ዌብሳይት፡- https://melcaethiopia.org/
ማህበራዊ ሚዲያ፡- MELCA-Ethiopia

MELCA-Ethiopia